# ይታደስ በዘመኔ

(ከእኔ -ዓለም)

የጥቁር ህዝብ ኩራት

ቀደምት የዘመናት

ከጉያዋ ወጡ ቀናተኛ ጠላት

ባንዳ የባንድ ልጅ አገሩን የከዳ

በዘር ተተብትቦ እውቀቱ የጓዳ

የግድ ይፈተናል በዘላለም ፍዳ

ታሪኬን ሳስበው የተከፈለ ነው ነፃ ነኝ ከዕዳ

ያንድነት የታሪክ የነፃነት ክብር

የሕዝቦች ማህተም ያንተነትህ ህብር

ዘር እምነት ያለየው የኖረው በፍቅር

እንዴት ይደከማል በማይረባ ዲስኩር።

በባንዲራ ፍቅር ስንት ጀግና ሞተ

አጥንታቸው ወጋኝ ህሊናን ሞገተ

እንቢ አለኝ ስሜቴ ወኔዬ ከተተ

ውስጤ ቢቀሰቀስ ቢነግረው ለጎኔ

በሽለላ ዜማ በቀረርቶ ቅኔ

ባንዲራውን ለብሶ የሞተው ወገኔ

መቼም አልረሳውም ታሪኬ ነው ለኔ

እንዲህ እኮራለሁ በጀግንነት ወኔ

ይቋጭ  ይህ ከሃዲ ጨካኝ አረመኔ

ይፈጸም ጨለማው የባንዳው ወያኔ

በክብር ይታደስ በእኔም በዘመኔ።